# ሀገራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ሰዎችና ተቋማት፣ ሀገር-በቀል የፈጠራ ሰዎች እና የልዩ ተሰጥኦ ባለቤቶች የሽልማት መመሪያ ቁጥር 567/2013

National Science and Technology Innovators and Institutions, Indigenous Innovators, and Owners of Special Talents Award Directive No. 567/2013

የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
Ministry of Science and Technology

ሚያዚያ 1፥ 2008

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

## 1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ "ብሔራዊ በሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ሰዎችና ተቋማት፣ ሀገር-በቀል የፈጠራ ሰዎችና እና የልዩ ተሰጥኦ ባለቤቶች የሽልማት መመሪያ ቁጥር **567/2013** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1. **"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው፣
2. **"ሀገር በቀል የፈጠራ ስራ"**ማለት በሀገራችን ባህልና ወግ እንዲሁም የአኗኗር ዘይቤ ተቀባይነት ኖሮት አዲስና ልዩ የሆነ የማህበረሰቡን ችግር ሊቀርፍ የሚችል ግኝት ወይም የአሰራር ስልት ማለት ሲሆን የባህላዊ ህክምናና መድኃኒት፣ ባህላዊ ቀዶ ጥገና ህክምና፣ ዋግምት፣ ባህላዊ የእንስሳት ህክምና፣ እደ ጥበባት፣ የግብርና ስልቶችና የአስተራረስ ዘዴዎች (በመሬት አጠቃቀምና ልማት፣ በአፈርና ውሃ ወይም ተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ)፣ በፀረ-ተባይ፣ በብረታ ብረት ማቅለጥና ቅርጽ ማውጣት ወይም ቀጥቃጭነትና አንጥረኛነት፣ በቆዳ ማለስለስ፣በቆዳ ውጤቶችና ሌጦ ስራዎች፣ በሽመና እና ጥልፍ ወይም ሹራብ ስራ፣ በጎጆ ኢንዱስትሪ፣ የስነ-ዕጽዋት መድኃኒት ቀመማና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፣
3. **"ልዩ ተሰጥዖ"** ማለት አንድን የሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ውጤት ወይም ስራ ወይም የአስተሳሰብ ወይም የአሰራር ስልት በሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታ ሲመዘን በተለየ ብቃት፣ ጥራትና ጊዜ በተሻለ ውጤት ወይም አሰራር ለመፈጸም የሚያስችል ክህሎት ወይም ዕውቀት ሲሆን በሳይንስና ቴክኖሎጂ የልዩ ተሰጥኦ ፈጠራን ወይም በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ ወይም በሂሳብ ዕውቀት ወይም ትምህርት ልዩ ተሰጥኦን ይጨምራል፣
4. **"ተቋማት"** ማለት ዩኒቨርስቲዎች፣ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋም፣ የምርምርና የማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ይመለከታል፣
5. **"ሳይንስ"** ማለት የነባራዊውን ዓለም እንዲሁም የተፈጥሮ ህግጋትንና ክስተቶችን ለማብራራትና ለመገንዘብ የሚያስችለንን እውቀት በምልከታና በሙከራ የምናገኝበት ዘዴ ወይም ስልት ነው፣

6. **"ቴክኖሎጂ"** ማለት የህብረተሰብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመቅረፍና የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የሚያስችል ከቁሳቁሶች አመራረትና አጠቃቀም ጋር የተጣመረ እውቀት ወይም የአደራረግ ጥበብ ወይም የአሰራር ዘዴና ሥርዓት ነው፣

7. **"ኢኖቬሽን ወይም ፈጠራ"** ማለት የተፈጠረ ቴክኖሎጂን የሚያሻሽል፤ ለነባር ቴክኖሎጂ አዲስ ጥሬ እቃ ምንጭ የሚሆን ወይም አዲስ ገበያ የማስገኘት ወይም በነባር ቴክኖሎጂ ላይ አዲስ ተጨማሪ በማከል ቴክኖሎጂው የተሻሻለ እና የቀለጠፈ ወይም በመሻሻሉ የተነሳ የማምረቻና የአገልግሎት ጊዜንና ወጪን የሚቀንስ ወይም ገበያነውን የሚያሰፋ ቴክኒካዊ የመፍትሄ ሀሳብ ነው፣

8. **"የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፎች"** ማለት የትምህርት ወይም የዕውቀት ዘርፍ ሆኖ የቴክኖሎጂና ኢንጂነሪንግ ሳይንሶችን፣ ግብርና ሳይንሶችንና የህክምናና የጤና ሳይንሶችን የሚያጠቃልል ነው፣

9. **"አዲስ"** ማለት የደንበኛን ወይም የተገልጋይን ፍላጎትን የሚያገበገ ወይም የሚስብ አዲስ የአመራረት ዘይቤ ወይም መንገድ ወይም አዲስ ምርት ወይም ስርዓት ወይም የአመራረት ሂደት የፈጠራ ኃሳብ ነው፣

10. **"የምርት ፈጠራ"** ማለት ለአጠቃቀም ምቹ የሆኑ አዲስ ወይም የተሻሻሉ ሸቀጣሸቀጥ እና ቁሳቁስ ማለት ነው፣

11. **"የአመራረት ሂደት ፈጠራ"** ማለት ምርትና አገልግሎትን በአዲስ አሰራር ወይም መንገድ ሲመረትና ለተጠቃሚው ሲሰራጭ ነው፣

12. **"ቴክኖሎጂ ላይ ለመስራት አስቻይ አካባቢያዊ ሁኔታዎች"** ማለት ተቋሙ አዲስ ሀሳብ እንዲያመነጭ ያለው ጠንካራ እምነትና ነፃነት ነው፣

13. **"የጥራት ሥራ አመራር"** ማለት ግብአቶችን በአግባቡና ውጤታማ በሆነ መንገድ በመጠቀም ለደንበኞች እና ለማህበረሰቡ አርኪ እንዲሁም ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት ማለት ነው፣

14. **"በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ግንኙነት"** ማለት ተቋማትና ግለሰቦች በጋራ ጥቅም መርህ ላይ በተመሰረተ ችግሮችን መፍታት መቻል ነው፣

15. **"ዘላቂነት ያለው የፈጠራ ስራ"** ማለት የፈጠራው ስራ ተከታታይነት ያለውና ችግር ፈቺ የሆነ ማለት ነው፡፡

16. **"በሀገር ደረጃ ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው የልማት ፕሮግራሞች"** ማለት በጨርቃጨርቅ፣ ብረታ ብረት፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ ኬሚካልና ምግብና መጠጦች፣

ፋርማሲቲካል፣ አግሮፕሮሰሲንግ፣ ባዮቴክኖሎጂ፣ ኢንፎርሜሽንና ኤሌክትሮኒክስ፣ በኮንስትራክሽን፣ በውሃ እና በሃይል ልማት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ማለት ነው፣

17. "የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ" ማለት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚሰየሙ የዕጩ ተሸላሚዎችን ወይም ተወዳዳሪዎችን ስራ መገምገም እና ውጤታቸውን ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚያሳውቅ ኮሚቴ ነው፣

18. "ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ" ማለት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አማካኝነት የሚቋቋም በውድድርና ሽልማት ሂደት ወቅት የሚነሱ ቅሬታዎችን በመቀበል የሚመረምርና የውሳኔ ሀሳብ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚያቀርብ አካል ነው፣

19. "ፆታ" በዚህ መመሪያ ለወንድ የተገለፀው አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል።

## 3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማዎች፡-

1. ለሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ቴክኖሎጂያዊ እድገት አስተዋፅኦ ያደረጉ የፈጠራ ስራ ለሰሩ ግለሰቦች እና ተቋማት፣ በሀገር በቀል የፈጠራ ስራ ላይ የተሰማሩትንና በልዩ ተሰጥዖ የተለዩ ግለሰቦችንና ተቋማት ዕውቅና እና ማበረታቻ ሽልማት በመስጠት ተስጥዖአቸው እንዲጎለብት ማድረግ፣
2. በህብረተሰቡ ውስጥ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ዝንባሌ እንዲሁም ልዩ ተሰጥኦ እንዲያድግና እንዲበረታታ በማድረግ ተጨባጭ እንቅስቃሴና ንቅናቄ እንዲፈጠር ማስቻል እና፣
3. በዘርፉ ሀገርበቀል የፈጠራ ስራዎችንና ልዩ ተሰጥኦዎችን ከዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር በማስተሳሰር ዘላቂነት ባለው መልኩ ለሀገር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም እንዲሰጡ ማስቻል ናቸው።

## 4. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሀገር ደረጃ ቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው የልማት ፕሮግራሞች ላይ ፈጠራ ባካሄዱ የፈጠራ ሰዎችና ተቋማት፣ በሀገር-በቀል የፈጠራ ስራዎችና የልዩ ተሰጥኦ ባለቤት በሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩና ኢትዮጵያዊ ዜግነት ባላቸው አካላት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## ክፍል ሁለት

## የተሸላሚዎች መመዘኛ መስፈርትና የሽልማትሂደት

### 5. የሽልማት ምድብ አይነቶች

በዚህ መመሪያ መሰረት የሚከተሉት ሶስት አካላት ተሸላሚ ይሆናሉ፡-

1. የፈጠራ ሰዎችና ተቋማት ምድብ፣
2. ሀገር-በቀል የፈጠራ ስራዎችና
3. የልዩ ተሰጥኦ ሽልማት ምድብ ሲሆኑ፡፡

የፈጠራ ሰዎችና ተቋማት ምድብ 3 ንዑስ የሽልማት ምድቦች ይኖሩታል፡፡

እነሱም፡-

1.የፈጠራ ተቋማት ሽልማት

2.የፈጠራ ሰዎች ሽልማት እና

3. የሴት የፈጠራ የሽልማት ምድብ ናቸው፡፡

### 6. የተወዳዳሪዎች አግባብነትና መምረጫ መስፈርት

በሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ሰዎችና ተቋማት ሽልማት ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉት፡-

1. የውጭ ቴክኖሎጂን በማላመድ ወይም በመኮረጅ ወይም የተወሰነ ማሻሻል ላይ የሰሩ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው የፈጠራ ሰዎች መሆን አለባቸው፣
2. በሀገር ውስጥ የሚገኙ የፈጠራና የምርምር ስራ የሚሰሩ የግልና የመንግስት የምርምር ተቋማትና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ መሆን አለባቸው፣
3. የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤትነት ሰርተፊኬት ማቅረብ የሚችሉ ግለሰቦችና ተቋማት፣
4. የፈጠራ ስራው ተግባራዊ የሆነና ለተጠቃሚው ተደራሽ የሆነ እንዲሁም ከተጠቃሚው ወይም ከተቋም የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችሉ ግለሰቦችና ተቋማት፣
5. የማምረቻና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ችግር የሚፈታ የፈጠራ ስራ ማቅረብ የሚችል፣
6. ተወዳዳሪዎች ለዚህ ውድድር የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ ሞልተው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 7. በሀገር-በቀል የፈጠራ ስራዎችና የልዩ ተሰጥኦ ሽልማት ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉት

1. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ሀገር በቀል ፈጠራ ስራ የሰሩ ኢትዮጵያውያን፤
2. በሳይንስና ቴክኖሎጂ የልዩ ተሰጥኦ ፈጠራ ላይ የተሰማሩ ወይም በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ ወይም በሂሳብ ዕውቀት ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ኢትዮጵያውያን፤
3. ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ ስራ ያልተሸለመና አዲስ የፈጠራ ወይም የልዩ ተሰጥኦ ስራ ያለው፣
4. ሁሉም እጩ ተወዳዳሪዎች ለውድድር የሚቀርቡት በዋናነት በሠሩት በአንድ የፈጠራ ወይም በሚያቀርቡት የልዩ ተሰጥኦ ስራ ወይም ዘርፍ ብቻ ይሆናል፤
5. የፈጠራ ስራው በተቋም ደረጃ የተሰራ ከሆነ ወይም ልዩ ተሰጥኦው በተቋም ተለይቶ እውቅና ከተሰጠው ከተቋሙ ድጋፍ ደብዳቤ መቅረብ አለበት፣
6. በግል ለሚቀርቡ በአካባቢያቸው ከሚገኘው የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት ወይም ልዩ ተሰጥኦው በግለሰብ ደረጃ ከአካባቢው አስተዳደር ወይም ማህበረሰብ አቀፍ ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
7. ተወዳዳሪዎች ሀገር በቀል እውቀትን ወይም ልዩ ተሰጥኦ በመጠቀም የላቀ የፈጠራ ውጤት ወይም ልዩ ተሰጥኦ ያስመዘገቡ ኢትዮጵያን መሆን ይኖርባቸዋል፣
8. አመልካቾቹ ባቅራቢያቸው ከሚገኝ አስተዳደር ወይም ተቋም ፈጠራው በራሱ ወይም በራስዋ ስለመሰራቱ ወይም ልዩ ተሰጥኦው በሚገኙበት ወይም በሚሰሩበት ወይም በሚማሩበት ተቋም ከአቻ ወይም መሰሎቻቸው ጋር በዘርፉ የልዩ ተሰጥኦ ምስክርነት (Recommendation) የተሰጣቸውና ችግር ፈች መሆኑን የሚረጋግጥና ስለ ስራው ዴጋፊ የሆኑ ሌሎች ማስረጃዎችና ሰነዶችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
9. ተወዳዳሪዎች ለዚህ ውድድር የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ ሞልተው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 8. ሌሎች ታሳቢ ጉዳዮች

1የተሰሩ የፈጠራ ሥራዎች ወይም ለቀረቡት ልዩ ተሰጥኦዎችና ባህላዊ እውቀቶች ደጋፊ ሰነዶችና ከተለያዩ አካላት የተሰጡ ማረጋገጫዎች ተያይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፣

2 ስራው የአካባቢውን ማህበረሰብ ችግር የሚፈታ መሆኑን የሚያረጋግጥ መስረጃ መቅረብ አለበት፣

3 ስራው የማህበረሰቡን ቋንቋ፣ ባህል እና እሴቶች የሚጠብቅ፤ የሚያስተዋውቅና የሚታደግ መሆን አለበት፣

4 ተወዳዳሪው በስራው የመጠቀምና የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ መስረጃ መኖር አለበት፣

5 በማህበረሰቡ ባህል የስራው ተቀባይነትና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት የተረጋገጠ መሆኑ፣

6 ስራው የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ሚዛንን የማያዛባና የአካባቢ ብክለት የማያስከትል መሆኑ፣

7. ፈጠራውን ለመስራት የሚጠቀምበት ግብአት በአካባቢው አቅም ሊሸፈን የሚችል መሆኑ፤

8 ሀገር በቀል የፈጠራ ስራው በቀላሉ በምርምርና ስርጸት ለማዳበር ወይም በማምረቻ ኢንዱስትሪ ለማሸጋገር ወይም ለማዘመን መቻሉ፣

9. ስራው በዘርፉ ያለውን የዕውቀት፣የክህሎት ወይም የፈጠራ አሰራር በመቀመር ያሻሻለ ወይም ያሳየ መሆኑ፣

10. በዘርፉ ወይም በዘርፉ ባለሙያዎች ያለው ተቀባይነትና ሳይንሳዊ አዋጭነት የተረጋገጠ መሆኑ፣

11.የፈጠራና የልዩ ተሰጥኦው ስርጭትና የተደራሽነት ወሰኑን ስፋት ያመላከተ መሆኑ፤

12 ባሉበት ተቋም ወይም በትምህርት ቤት፤ በዩኒቨርሲቲ፤ በአካባቢ ደረጃ በሳይንስና ቴክኖሎጂ በልዩ ተሰጥኦ የተሸለሙ ወይም እውቅና ያገኙ፣

13 ካሁን ቀደም በዘርፉ በተለያዩ ተቋማት የተዘጋጁ የልዩ ተሰጥኦ መመዘኛ ወይም መለኪያ ተመዝነው ማረጋገጫ የተሰጣቸው፣

14. ተወዳዳሪዎቹ በሚገኙበት ወይም በሚሰሩበት ወይም በሚማሩበት ተቋም ከአቻ ወይም መሰሎቻቸው ጋር በዘርፉ ስልዩ ተሰጥኦ ምስክርነት (Recommendation) የተሰጣቸው፣

15. በተጨማሪም ለዚህ ውድድር የሚቀርበውን የተግባርና የንድፈ-ሀሳብ መመዘኛ ዝቅተኛ መስፈርት ወይም መለኪያ ፈተና(challenge) ማለፍ የሚችሉ ሲሆን፣

16. ተወዳዳሪው ለሚያቀርበው ልዩ ተሰጥኦ በተለያዩ ጊዜያት ለተሰሩ ስራዎች ብዛትና አይነት ማረጋገጫ ሰነዶችን ማቅረብ የሚችል፣

17. ተወዳዳሪው ልዩ ተሰጥኦውንና ስራዎቹን ለገምጋሚ ኮሚቴ በብቃትና በጥራት ማቅረብና ማስረዳት ይኖርበታል፣

18. ሴት ተወዳዳሪዎች ወይም አካል ጉዳተኞች በውድድሩ ካገኙት ነጥብ በተጨማሪ ሶስት ነጥብ (Affirmative action) ይደመርላቸዋል፤ ሴት ተወዳዳሪዎች ከወንዶች ጋር

እንዲሁም አካል ጉዳተኞች ከሌሎች ጋር ሲወዳደሩ እኩል ነጥብ ካገኙ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፣

19. ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ ላይ በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሠረት ያልተገለጹ ስራዎች ዋጋ አይኖራቸውም፡፡

## 9. የመምረጫ መስፈርቶች ሌሎች የዚህ መመሪያ አካል የሆኑ አባሪዎች

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የሚውሉ የማመልከቻ ቅጽ፤ የአመልካቾች ማጠቃለያ፤ የመምረጫ መስፈርት፡ በእያንዳንዱ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ክብደት ተሰጥቷቸው የተመላከቱ ሲሆን ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ መስፈርቶች ተያይዘዋል፡፡

## 10. የሚሰጠው ሽልማት

ለሁሉም ውድድር አሸናፊዎች በየደረጃው፡-

1. ሰርቲፊኬት፣
2. ሜዳሊያ (የነሃስ ወይም የብር ወይም የወርቅ)፣
3. የገንዘብ ሽልማት የሚሰጥ ይሆናል፡፡
4. ለተቋማትም በተመሳሳይ እንደየደረጃቸው ሰርቲፊኬት፣ ዋንጫ እንዲሁም የገንዘብ ሽልማት የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

# ክፍል ሶስት

## የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ስለማቋቋምና የኮሚቴው ተግባርና ሀላፊነት

## 11. የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ስለማቋቋም

1. የሚቋቋመው ኮሚቴ ሶስቱንም ዋና ዋና የሽልማት ምድቦች ዘርፎችን ባማከለ መልኩ ከተለያዩ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተቋማት፣ ከሚመለከታቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ ኤጀንሲዎችና ሊሎች ተቋማትና ድርጅቶች የተውጣጡ ሆነው በዘርፉ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ግለሰቦችን የያዘ ይሆናል፤ እነዚህ አካላትም በአባሪ 5 ላይ በዝርዝር ተመላክተዋል፤
2. የኮሚቴው ሊቀመንበር እና እንደ አስፈላጊነቱም ምክትል ሊቀመንበር ከኮሚቴው አባላት ውስጥ የሚመረጥ ይሆናል፣
3. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ተወካይ የኮሚቴው ፀሀፊ ሆኖ ያገለግላል፣

4. የፈጠራ ሰዎችና ተቋማት፤ የልዩ ተሰጥኦ ባለቤቶችና ሀገር-በቀል የፈጠራ ሰዎች ገምጋሚና መራጭ የሽልማት ኮሚቴ አባላት ከመንግስትና ከግል ተቋማት እንዲሁም ከሳይንስ ሙያ ማህበራት የተውጣጡ አባላት የሚወክሉ ሲሆን በተጨማሪም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሙያው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ግለሰቦች ዕጩ ተወዳዳሪዎችን በአግባቡ ለመለየትና ለመምረጥ ኮሚቴውን የሚያግዙ ይሆናል።

5. የፈጠራ ሰዎችና ተቋማት፤ የልዩ ተሰጥኦ ባለቤቶችና ሀገር-በቀል የፈጠራ ሰዎች ግምገማና መረጣ በበላይነት የሚያስፈጽም ብሔራዊ የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ በዋናነት አባሪ በተደረገው የባለድርሻ አካላት ዝርዝር መሰረት በማውጣጣት ይቋቋማል።

## 12. የኮሚቴው ተግባር እና ኃላፊነት

ኮሚቴው፡-

1. የተወዳዳሪዎችን ማመልከቻ በመመሪያው ላይ ባለው መስፈርት መሰረት የሚገመግም ይሆናል፣
2. ኮሚቴው የተወዳዳሪዎችን ውጤት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለውሳኔ ያቀርባል፣
3. ኮሚቴው የሽልማት መመሪያው እንዲከለስ የማሻሻያ ሀሳብ/ግብአት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያቀርባል፣
4. በሽልማት ምድቡ የቀረቡ ተወዳዳሪዎች ሰነድ ትክክለኛነት ያረጋግጣል፣
5. በግምገማ ወቅት በየዘርፉ አጠቃላይ የሽልማት መስፈርቱን ሊያገዙ የሚችሉ ተጨማሪ ደረጃቸውን የጠበቁ መመዘኛዎችን ወይም ፈተና (challenge) በጋራ በማዘጋጀት ዕጩ ተሸላሚዎችን መመዘን ይችላል፣
6. በተወዳዳሪዎች የተሰሩ የፈጠራ እና የቀረቡ የልዩ ተሰጥኦ ስራዎችን በመስፈርቶቹ መሰረት በመገምገም በሀገር አቀፍ ደረጃ ውጤት ይሰጣሉ፤ ለሽልማት ብቁ የሆኑትን በደረጃ ለይቶ ያቀርባል፣
7. የተመረጡትን እጩ ተሸላሚዎችን የአመራረጥ ሂደትና ውጤት ሪፓርት ለሚኒስቴሩ የበላይ አመራር በማቅረብ ያፀድቃል።

## 13. የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት

ሚኒስቴሩ፡-

1 በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው ሽልማት በጀት ያስመድባል፣
2 ሽልማቱ ከመካሄዱ 4 ወራት በፊት በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ጥሪ ያደርጋል፣
3. ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤ እንዲተባበሩም ጥያቄ ያቀርባል፣

4. በሽልማት አፈጻጸም ላይ ክትትል ያደርጋል፣
5. በሽልማት ምድቡ የሚቀርቡ ተወዳዳሪዎችን መረጃ በማደራጀት ለብሄራዊ ገምጋሚ ኮሚቴ አባላት ዝግጁ ያደርጋል፣
6. በገምጋሚ ኮሚቴ ተገምግሞ የቀረበውን የተወዳዳሪዎች መረጃ አግባብነት በማረጋገጥ ያጸድቃል፣
7. የተሸላሚዎችን መረጃ ያደራጃል፤ ያሰራጫል፤
8. የላቀ ውጤት ላስመዘገቡት ተሸላሚዎች የማበረታቻ ሽልማት ይሰጣል፣
9. የሽልማቱን ሂደት በአህዝቦት ስራዎች በማስደገፍ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆን ይሰራል፣
10. ለውድድር የተዘጋጁትን መመሪያዎች፣ መስፈርቶችንና ማስታወቂያዎችን ተደራሽ እንዲሆኑና ስራዎችን ለማሰባሰብ እንደአስፈላጊነቱ የመስክና የመረጃ ዳሰሳ ያካሂዳል፣
11. እንደሁኔታው ለተሸላሚዎች የትስስርና የስልጠና ማበረታቻዎችን ያመቻቻል።

## 14. የኮሚቴው የስራ ጊዜ

ኮሚቴው የተወዳዳሪዎችን ስራዎች ለመገምገምና ለመምረጥ በአመት እስከ ስምንት ጊዜ የሚሰበሰብ ይሆናል። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም የስብሰባውን መርሀ-ግብር ለአባላቱ የሚያሳውቅ ይሆናል።

## ክፍል አራት

## የማመልከቻ አቀራረብ፣ የአመራረጥ ሂደት፣ ውጤት ማሳወቅ እና ከውድድር ወጭ የሚሆንበት ጉዳይ

## 15. የማመልከቻ አቀራረብ

1. የፈጠራ ሰዎች ስራዎቻቸውን ለውድድር እንዲያቀርቡ በሚኒስቴሩ በኩል በመገናኛ ብዙሃን በሚደረገው ጥሪ ጊዜ ሰሌዳ መሰረት ማመልከት አለባቸው፣
2. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለአመልካቾች የማመልከቻ ቅፁን ወይም ፎርሙን እንዴት እንደሚመሉትና ስለአጠቃላይ የሽልማት አካሄዱ ገለፃ የሚሰጥ ይሆናል፣
3. አመልካቹ የተሟላ የድጋፍ ሰነዶችን ማለትም የአዕምሯዊ ጥበቃ ባለቤትነት ሰርቲፊኬት ከተጠቃሚው የሚሰጥ የድጋፍ ደብዳቤና ሌሎች አስፈላጊ መስረጃዎችን አያይዞው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

## 16. የማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜ

ማመልከቻ የማቅረቢያ ጊዜ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚወሰንና በመገናኛ ብዙኃን የሚገለጽ ሲሆን አመልካቾች በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊ መረጃዎችን አሟልተው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 17. ከውድድር ውጭ የሚሆንበት ጉዳይ

1. አመልካቹ አስፈላጊና ደጋፊ መረጃዎችን አሟልቶ ካላቀረበ፣
2. ከዚህ በፊት በተደረጉ ተመሳሳይ የውድድር ሽልማቶች ላይ ከቀረቡና በተመሳሳይ ስራዎች ተሸላሚ ከነበር ከውድድር ውጭ ይደረጋል፡፡

## 18. የተሸላሚዎች አመራረጥ ሂደት

1. ተወዳዳሪዎች ሚኒስቴሩ ለዚህ ውድድር ያዘጋጀውን ማመልከቻ ቅጽ በአግባቡ ሞልተው እንዲሁም የስራዎችን ዝርዝር መግለጫና ማብራሪያ የያዘ ፕሮፖዛል እና ተያያዥ ደጋፊ ሰነዶችን በማያያዝ በአካል በመቅረብ ይመዘገባሉ፣
2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቀረቡ ተወዳዳሪዎችን የፈጠራ ስራዎችንና ሰነዶችን በማደራጀት ቅድመ-ማጣራት በማድረግ ለሀገር አቀፉ ገምጋሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣
3. ኮሚቴው በዚህ የሽልማት መመሪያ መሰረት በማድረግ የቀረቡትን የተወዳዳሪዎችን ማስረጃዎችና ሰነዶችን በጥልቀት ይገመግማሉ፣
4. ኮሚቴው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተወዳዳሪዎች ስራዎቻቸውን በአካል እንዲያቀርቡና እንዲያስረዱ በማድረግ በደረጃ በመለየት ይመርጣሉ፣
5. የገምጋሚ ኮሚቴው የግምገማውን ውጤት ከአስፈላጊ መረጃዎች ጋር ለሚኒስትሩ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣
6. የተመረጡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በሚኒስቴሩ የበላይ አመራር ይሁንታን አግኝተው ሲጸድቅ የተሸላሚዎች ውጤት ይፋ ይደረጋል፣
7. ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አሸናፊዎችን በሚያዘጋጀው የሽልማት ስነ-ስርአት እውቅና በመስጠት ማበረታታት ያደርጋል፡፡

## 19. የውድድር ዝርዝር መስፈርቶች ወይም ቼክ-ሊስት

በግል የሚወዳደሩ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ወይም ተቋምን ወክለው የሚወዳደሩ ዕጩ ተወዳዳዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የውድድሩ ዝርዝር መስርቶች ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ተደርጎ ተያይዞል፡፡

## ክፍል አምስት

## የቅሬታ አቀራረብ ስርአት

### 20. የቅሬታ አቀራረብ ቅድመ-ሁኔታዎች

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሚያቋቁም ሲሆን ተወዳዳሪዎች በእኩልነትና በፍትሀዊነት እንዲወዳደሩ እንዲሁም የተወዳዳሪዎች መረጃ/ስራዎቻቸው በአግባቡ በተቋሙ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡ ሆኖም ግን እነዚህ ሁኔታዎች ሲጣሱ ተወዳዳሪዎች ቅሬታቸውን ለተቋቋመው ኮሚቴ በማቅረብ የሚፈታ ይሆናል፡፡

### 21. ቅሬታ አቀራረብ

ቅሬታ አቅራቢው በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ስራውን ለሚመራው ክፍል በጽሁፍ በአስር ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

### 22. ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ

1. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኮሚቴውን የሚያቋቁም ይሆናል፣
2. የኮሚቴው አባላት፣

2.1. የሳይንስና ተክኖሎጂ ሚኒስቴር የበላይ አመራር ተወካይ..........ሰብሳቢ

2.2. በሚ/ር መ/ቤቱ ስራውን የሚመራው ክፍል ..........................ፀሀፊ

2.3. የሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ሰብሳቢ/ም/ሰብሳቢ............አባል

2.4. የህግ ጉዳዮች ..................................................................አባል

2.5. የስነ-ምግባር የስራ ክፍል......................................................አባል

3. ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ቅሬታ አቅራቢው በአስር ቀናት ውስጥ በፁሁፍ ማቅረብ ካልቻለ ቅሬታውን ውድቅ ማድረግ ይችላል፣

4. ኮሚቴው የቅሬታ አቅራቢውን መረጃዎች እንዲሁም ማመሳከሪያዎችን በአግባቡ ይመረምራል፣

5. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ውሳኔ ለመስጠት እንዲያስችለው ከሽልማት ገምጋሚ ኮሚቴው ጋር በቅሬታው ላይ በዝርዝር ይወያያል፣
6. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው የመነሻ ውሳኔውንና አስያየት በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው ያሳውቃል፣
7. ኮሚቴው የቅሬታ አፈታቱን የውሳኔ ሀሳብ እና አስተያየት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያሳውቃል፣
8. የመጨረሻ ውሳኔ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 23. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መመሪያውን ሊያሻሽለው ይችላል።

### 24. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

መጋቢት ............ ቀን 2008 ዓ.ም

አብይ አህመድ

ሚኒስትር

አብይ አህመድ
ሚኒስትር

## 25. አባሪዎች

### አባሪ 1

1. የግለሰብ የፈጠራ ስራዎች እና/ወይም የሴት የፈጠራ ሰዎች የመምረጫ መስፈርቶች

| ተ.ቁ | የመገምገሚያ መስፈርቶች | ለመስፈርቱ የተሰጠው ክብደት በፐርሰንት | በየመስፈርቱ ለተወዳዳሪው የተሰጠው ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | ጠቀሜታ<br>i. ከማህበራዊ ጠቀሜታ አንፃር<br>• የህብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ የሚያሻሽል ከሆነ<br>• የስራ ዕድል የሚፈጥር ከሆነ<br>• የሴትን የስራ ጫና የሚቀንስ ከሆነ<br>• አካል ጉዳተኞችን የሚጠቅም ከሆነ | 40<br>10 | |
| 0 | ii. ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንፃር<br>• የገቢ ምርትን የሚተካ የፈጠራ ስራ ከሆነ<br>• የወጪ ምርትን የሚያሳድግ ፈጠራ ከሆነ<br>• የፈጠራ ስራው ድህነት ቅነሳ ላይ አወታዊ ተፅዕኖ ካለው | 20 | |
| 0 | iii. ከአካባቢ ልማትና ጥበቃ አንፃር<br>• ቆሻሻና አካባቢ መበከልን የሚቀንስ የፈጠራ ስራ ከሆነ<br>• በአግባቡ የተፈጥሮ ሀብትን መጠቀምና ሃይልን መቆጠብ የሚያስችል የፈጠራ ስራ ከሆነ | 10 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2 | የፈጠራ ስራው ሁኔታ<br>• የደንበኞችን ፍላጎት በጥራት ደረጃ የሚያሟላ ከሆነ<br>• ወጪ ቆጣቢነት<br>• በአጭር ጊዜ እንዲሁም ወጭ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ውጤት የሚያስመጣ ከሆነ<br>• በቀላሉ ሊተገበር የሚችል የፈጠራ ስራ ከሆነ<br>• ሀገር በቀል ዕውቀትንና ቴክኖሎጂን የሚያሻሽል ከሆነ | 20 | |
| 3 | ተግባራዊነት<br>• በትግበራ ለሁሉም የስራ ክፍሎች/Sectors /ተስማሚ የሆነ<br>• በሁሉም አካባቢዎች ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ከሆነ | 15 | |
| 4 | የመጀመሪያ/ቀዳሚ ስራ ከሆነ<br>• አዲስ ሀሳብ ወይም የተሻሻለ / የተኮረጀ ቴክኖሎጂ ከሆነ<br>• ለኢትዮጵያ ልዩ የሆነ የፈጠራ ስራ የሆነ<br>• በሳይንሳዊ መንገድ የተረጋገጠ ቴክኖሎጂ ከሆነ | 15 | |
| 5 | የሚቀዳና ቀጣይነት ያለው የፈጠራ ስራ<br>• በሌሎች ተቋማት/ኢንተርፕራይዞች መቀዳት የሚችል የፈጠራ ስራ ከሆነ<br>• ዋናው የመጀመሪያው ስራ ሌሎች እንዲቀዱት/prototype/ ያለው የፈጠራ ስራ ከሆነ<br>• ቀጣይነት ያለው የፈጠራ ስራ | 10 | |

ማሳሳቢያ፡

ለሴት ወይም አካል ጉዳተኛ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተጨማሪ ሶስት ነጥብ የማበረታቻ ውጤት(Affirmative action) ይደመርላቸዋል። ለፈጠራ ሰዎች እና ተቋማት ዝቅተኛ የማለፊያ ነጥብ 75% ሲሆን ለሴቶች ደግሞ 70% ነው።

አባሪ 2

## 2. የፈጠራ ተቋማት ለመሸለም የመምረጫ መስፈርቶች

| ተ.ቁ | የመገምገሚያ መስፈርቶች | ለመስፈርቱ የተሰጠው ክብደት በፐርሰንት | በየመስፈርቱ ለተወዳዳሪው የተሰጠው ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | የልዩ ፈጠራው ጠቀሜታ<br>I. ከማህበራዊ ጉዳዮች አንፃር<br>• የህብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ የሚያሻሽል ከሆነ<br>• የገቢ ምንጭነት<br>• የስራ ዕድል የሚፈጥር ከሆነ<br>• ለሴችን እና ለአካል ጉዳተኞች አመቺ እና የስራ ጫናን የሚቀንስ ከሆነ | 50<br>15 | |
| 2 | II. ከኢኮኖሚ አንፃር<br>• የገቢ ምርትን የሚተካ የፈጠራ ስራ ከሆነ<br>• የወጪ ምርትን የሚያሳድግ ፈጠራ ከሆነ | 20 | |
| 3 | III. ከአካባቢ ልማትና ጥበቃ አንፃር<br>• አካባቢን ከመጠበቅና ከማልማት አንፃር<br>• ዘላቂነት ያለው የተፈጥሮ ሀብትን አጠቃቀም እና ማልማት | 15 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2 | የቴክኖሎጂ አቅም<br>• ቴክኖሎጂን ካለው ተቀባይነት አንፃር<br>• ቴክኖሎጂን ከመረዳት አንፃር<br>• ቴክኖሎጂን ከማላመድ አንፃር | 15 | |
| 3 | የጋራ ተጠቃሚነትን ከማስፋት አንፃር ያለው ትስስር<br>• ከአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች<br>• ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች<br>• ከማህበረሰብ ልማት ድርጅቶች<br>• በጋራ ምርምር (በሀገር ውስጥ/ በውጭ ሀገር)<br>• ከከፍተኛ ት/ት ተቋማት እና ቴ/ሙ/ት/ስ ኮሌጆች | 12 | |
| 4 | የተቋማትን የስራ አመራር ብቃት ከማሳደግ አንፃር<br>• ደንበኛ ተኮር<br>• አመራር ሰጭነት<br>• የስራ ሂደት ፍሰት<br>• የአሰራር ስርአት ያለው<br>• ተከታታይነት ያለው መሻሻል<br>• አሳታፊነት | 6 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5 | የፈጠራ ስራው ተደራሽነት /ስርጭት<br>• የፈጠራው ስራው ፕሮቶታይፕ/ሞዴል ያለው መሆኑ<br>• አውደ ርዕይ ላይ የቀረበ<br>• ሀገራዊ አውድ ጥናት ላይ የቀረበ<br>• ከሌሎች ተቋማት ጋር የትስስር ተሞክሮ ያለው<br>• ፈጠራውን በተለያዩ የሚዲያ ውጤቶች ያስተዋወቀ | 8 | |
| 6 | ስፈጠራ ስራው ያሉ አስቻይ/አበረታች ሁኔታዎች<br>• የሽልማት እና የማበረታቻ ስርአት መኖሩ<br>• የተመቻቹ የግብአት እና የመሰረተ ልማት አቅርቦት መኖራቸው<br>• ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች መኖራቸው | 9 | |

አባሪ 3

## 3.የሀገር በቀል ፈጠራዎች መምረጫ መስፈርቶች

| ተ.ቁ | የሀገር በቀል መስፈርት | ለመስፈርቱ የተሰጠው ክብደት በፐርሰንት | በየመስፈርቱ ለተወዳዳሪው የተሰጠው ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | የተወዳዳሪው የትምህርት ደረጃ | 10 | |
| | • የመጀመሪያ ዲግሪና በላይ | 5 | |
| | • ዲፕሎማ | 2 | |
| | • የ2ኛ ደረጃ ትምህርትን ያጠናቀቀ/ች | 2 | |
| | • የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ያለው | 1 | |
| 2 | ፈጠራው በማህበረሰቡ ያለው ተቀባይነት | 10 | |
| | • በጣም ከፍተኛ | 5 | |
| | • ከፍተኛ | 3 | |
| | • መካከለኛ | 2 | |
| 3 | የሀገር በቀል የፈጠራ ስራው ይዘት | 20 | |
| | • ሙሉ በሙሉ ልዩና አዲስ | 8 | |
| | • የስራው ግብዓት ሙሉ በሙሉ በአካባቢው የሚሸፈን | 6 | |
| | • የፈጠራ ስራው ስርጭት ስፋት ወይም ተደራሽነት /ወደ ስራ የገባ | 6 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4 | ለግኝቱ የተሰጠ ማረጋገጫ<br>• ለሀገር በቀል ፈጠራነቱ ከሚመለከታቸው ማረጋገጫ ያለው<br>• ከሚኖሩበት አካባቢ አስተዳደር አካል/ማህበረሰባዊ ተቋም ድጋፍ ያገኘ<br>• ከሚመለከተው መ/ቤት የባለቤትነት ሰርቲፊኬት/ማስረጃ ያለው | 15<br>6<br>5<br>4 | |
| 5 | ለተጠቃሚዎችና ለአካባቢው ማህበረሰብ የሚሰጠው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ<br>• በጣም ከፍተኛ<br>• ከፍተኛ<br>• መካከለኛ | 10<br>5<br>3<br>2 | |
| 6 | ፈጠራው በቴክኖሎጂ ለማባዛትና ለማሻሻል ያለው አቅም<br>• በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማዘመን የሚችል<br>• ለመረዳት ውስብስብ ያልሆነ<br>• የጥሬ ግብዓት በቀላሉና በአቅራቢያ የሚገኝ | 10<br>5<br>3<br>2 | |
| 7 | የፈጠራው ስፋትና ተደራሽነት<br>• በሀገር አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ያለው<br>• በክልል ደረጃ ዕውቅና ያለው<br>• በወረዳ/ዞን/አካባቢ ደረጃ እውቅና ያለው | 15<br>6<br>5<br>4 | |
| 8 | የአጠቃቀምና የአሰራር ሁኔታና ስርጭት/ብዜት<br>• ግልፅ የሆነ የአዘገጃጀት/ የአጠቃቀምና የአሰራር መመሪያ | 10 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ያለው<br>• ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ መቅረብ የሚችል<br>• በቴክኖሎጂ ለማዘመንና ለማባዛት የሚያስችል | 4<br>3<br>3 | |

Ministry of Science and Technology
The Federal Democratic Republic of Ethiopia

አባሪ 4

## 4. የልዩ ተሰጥኦ መምረጫ መስፈርቶች

| ተ.ቁ | የልዩ ተሰጥኦ መስፈርት | ለመስፈርቱ የተሰጠው ክብደት በፐርሰንት | በየመስፈርቱ ለተወዳዳሪው የተሰጠው ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | የልዩ ተሰጥኦ አቅራቢው/ባለቤት የትምህርት ደረጃ<br>• የመጀመሪያ ዲግሪና በላይ<br>• ዲፕሎማ<br>• የ2ኛ ደረጃ ትምህርትን ያጠናቀቀ<br>• የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ያለው | 10<br>5<br>2<br>2<br>1 | |
| 2 | በሳ.ቴ ዘርፍ የልዩ ተሰጥኦው አይነትና ደረጃ<br>• የፈጠራ ወይም የምርት ተሰጥኦ/ Product Innovation Talent<br>• የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግና የሂሳብ ዕውቀት ተሰጥኦ/STEM Talent<br>• የአሰራር ክህሎት ተሰጥኦ /Technical Innovation Talent | 20<br>8<br>6<br>6 | |
| 3 | ልዩ-ተሰጥኦው በዘርፉ (ተቋም/ት/ቤት/ ዩኒቨርሲቲ/ አካባቢው) ያለው ተቀባይነት<br>• በጣም ከፍተኛ(ሙሉ በሙሉ)<br>• ከፍተኛ(በከፊል)<br>• መካከለኛ(በተወሰነ) | 15<br>6<br>5<br>4 | |
| 4 | የልዩ ተሰጥኦው ውህደት<br>• የፈጠራ ልዩ ተሰጥኦ (የፈጠራ፣ የክህሎትና የእውቀት) | 15<br>6 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | • የዕውቀት ልዩ ተሰጥኦ (የፈጠራና የዕውቀት)<br>• የክህሎት ልዩ ተሰጥኦ (የክህሎት) | 5<br>4 | |
| 5 | የልዩ ተሰጥኦው ቴክኖሎጂያዊና ሳይንሳዊ ይዘት<br>• ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ(ሙሉ በሙሉ)<br>• ሳይንሳዊ(በከፊል)<br>• ቴክኖሎጂያዊ(በተወሰነ) | 10<br>5<br>3<br>2 | |
| 6 | ለልዩ ተሰጥኦው የቀረበ ማረጋገጫ<br>• ከሚመለከተው ተቋም በዘርፉ የተሰጠ የምስክር ወረቀት/ ሰርቲፊኬት<br>• በሚገኙበት ተቋም/ድርጅት ደረጃ የተሰጠ የዕውቅና ማስረጃ<br>• ከሚኖሩበት የአካባቢ አስተዳደር አካል ወይም ት/ቤት ድጋፍ ያለው | 5<br>2<br>2<br>1 | |
| 7 | ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ለዘርፍ የሚኖረው አስተዋጽኦና ፋይዳ<br>• በጣም ከፍተኛ<br>• ከፍተኛ<br>• መካከለኛ | 10<br>5<br>3<br>2 | |
| 8 | የልዩ ተሰጥኦው ተደራሽነት<br>• በአለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ያለው<br>• በሀገር አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ያለው<br>• በተቋም/አካባቢ ደረጃ እውቅና ያለው | 5<br>3<br>1<br>1 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 9 | የልዩ ተሰጥኦው የአጠቃቀም ሁኔታና ደረጃ | 10 | |
| | • ግልፅ የሆነ የአዘገጃጀት/ ቀመር ያለው | 4 | |
| | • በዘርፉ መመዘኛ /መለኪያ ሊፈተሽ የሚችል | 3 | |
| | • በመሰሎች ሊተገበር የሚችል | 3 | |

- STEM፡- science,Technology,Engineering & Mathimatics

## አባሪ 5

**የፈጠራ ሰዎችና ተቋማት፣ የልዩ ተሰጥኦ ባለቤቶች እና ሀገር-በቀል የፈጠራ ሰዎች ሽልማት ገምጋሚና መራጭ ኮሚቴ ባለድርሻ አካላት**

| ተ.ቁ | ባለድርሻ ተቋማት |
|---|---|
| 1. | የኮሚቴው ፀኃፊ የሚኒስቴሩ ተወካይ |
| 2. | ከፌደራል ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ |
| 3. | ከትምህርት ሚኒስቴር |
| 4. | ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር |
| 5. | ከውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር |
| 6. | ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዮት |
| 7. | ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት |
| 8. | ከኢትዮጵያ ብረታብረት፣ ቆዳ እናጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቶች |
| 9. | ከኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት |
| 10. | ከኤሌክትሪካል መሃንዲሶች ሙያ ማህበር |
| 11. | ከኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት |
| 12. | ከኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር |
| 13. | ከአካባቢ ጥበቃና ከደን ልማት ሚኒስቴር እና ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሙያ ማህበራት |
| 14. | ከኢትዮጵያ የማህበረሰብ ጤና ኢንስቲትዩት |
| 15. | ከፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ አጀንሲ |
| 16. | ከኢትዮጵያ እደ-ጥበባት ባለሙያዎች ማህበር |
| 17. | ከባህልና ቱሪዝም ሚ/ር |
| 18. | የምግብ ፋርማስቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲቲት |
| 19. | የመድሀኒት ቁጥጥር ባለስልጣን |
| 20. | ከቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት |
| 21. | ከጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትትዮት |
| 22. | ከግብርና ምርምር ኢንስቲትዮት |
| 23. | ከሳቴ ጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት የተውጣጡ |
| 24. | ከኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ |
| 25. | ከኢትዮጵያ ኢንተርፕራነርሽፕ ዲቨሎፕመንት ማዕከል |
| 26. | የኢትዮጵያ ኢኖቬተርስ እና ኢንቬንተርስ አሶሴሽን |

➢ እንደአስፈላጊነቱ ስራው ጋር ተያያዥነት ካላቸው አጋር ተቋማትና የሳይንስና ቴክኖሎጂ የሙያ ማኅበራት ሕዝባዊ ክንፍ/ እንደ አስፈላጊነቱ የሚወከሉ አባላት ይኖሩታል።

## አባሪ 6

## በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

## በሀገር አቀፍ የፈጠራ ስራ የሰሩ ግለሰቦችንና ተቋማትን ለመሸለም የተዘጋጀ የማመልከቻ ቅፅ

ፓ.ሳ.ቁ፡ 2490 ስልክ ቁጥር፡ 0118-962290 / 0911-477477 / 0913089655

ፋክስ፡ 011-4-66 02 41 / 011-4-169533

የኢሜል አድራሻ፡most@ethinet.et/innvmost@gmail.com

ዌብሳይት፡http:/www.gov.et

1. የዕጩ ተወዳዳሪው ግላዊ መረጃ

    - ስም እስከ አያት፡-.......................................................

    - ፆታ፡- ወንድ...... ሴት.........

    - አድራሻ፡-

ስልክ ቁጥር፡ የሞባይል፡..................... መደበኛ፡.......................

ክልል፡-.............................

ከተማ/ወረዳ፡-.....................

ፋክስ ቁጥር፡-.............................

ኢሜል፡-...................................

2. የትምህርት እና የስራ ሁኔታ

የትምህርት አይነት፡-............................

የትምህርት ደረጃ፡-.............................

አሁን እየሰሩበት ያለው

ተቋም፡-………………

የስራ ሃላፊነት፡-………..

የስራ ልምድ፡-………….

3. ለውድድር ያቀረቡት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፎች ውስጥ በሚከተለው ያመላክቱ

☐ በቴክኖሎጂና ኢንጂነሪንግ ሳይንስ

☐ በተፈጥሮ ሳይንስ

☐ በግብርና ሳይንስ

☐ በህክምና እና በጤና ሳይንስ

4. የፈጠራው/ስራው ርዕስ፡- ………………………………………………………………………

5. የፈጠራው/ስራው ውጤት መግለጫ

የግለሰቦች የፈጠራ የሽልማት መስፈርቶች

ከዚህ በታች በተመላከተው ዝርዝር መስፈርት መሰረት የግለሰቦች የፈጠራ የስራ ውጤት ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

| ተ.ቁ | የመገምገሚያ መስፈርቶች | ለመስፈርቱ የተሰጠው ክብደት |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| 1 | የፈጠራው ጠቀሜታ | 40 |
| | ፤. ከማህበራዊ ጉዳዮች አንፃር<br>• የህብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ የሚያሻሽል ከሆነ<br>• የስራ ዕድል የሚፈጥር ከሆነ<br>• የሴችን የስራ ጫና የሚቀንስ ከሆነ<br>• አካል ጉዳተኞችን የሚጠቅም ከሆነ | 10 |
| | ፤፤. ከኢኮኖሚ አንፃር<br>• የገቢ ምርትን የሚተካ የፈጠራ ስራ ከሆነ<br>• የወጪ ምርትን የሚያሳድግ ፈጠራ ከሆነ<br>• የፈጠራ ስራው ድህነት ቅነሳ ላይ አወታዊ ተዕዕኖ ካለው | 20 |
| | ፤፤፤. ከአካባቢ ልማትና ጥበቃ አንፃር<br>• ቆሻሻና አካባቢ መበከልን የሚቀንስ የፈጠራ ስራ ከሆነ<br>• በአግባቡ የተፈጥሮ ሀብትን መጠቀምና ሃይልን መቆጠብ የሚያስችል የፈጠራ ስራ ከሆነ | 10 |
| 2 | የፈጠራ ስራው ባህሪ<br>• የደንበኞችን ፍላጎት በጥራት ደረጃ የሚያሟላ ከሆነ<br>• ወጪ ቆጣቢነት<br>• የፈጠራው ስራ የአመራረት ብቃትን ያሻሻለ<br>• በቀላሉ ሊተገበር የሚችል፣ ተስማሚ፣ ሊጠገን እና ሊተካ የሚችል የፈጠራ ስራ ከሆነ<br>• ሀገር በቀል ዕውቀትንና ቴክኖሎጂን የሚያሻሽል ከሆነ | 20 |

| | | |
|---|---|---|
| 3 | ተግባራዊነት<br><br>• ለተለያዩ ዘርፎች /Sectors / ለመጠቀም አመቺ የሆነ<br><br>• በሁሉም አካባቢዎች ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ከሆነ | 15 |
| 4 | የፈጠራው አዲስነት<br><br>• አዲስ ሀሳብ ወይም የተሻሻለ / የተከረጀ ቴክኖሎጂ ከሆነ<br><br>• በኢትዮጵያ ልዩ የሆነ<br><br>• በሳይንሳዊ የአሰራር ዘዴ የተከተለ/የተረጋገጠ ቴክኖሎጂ ከሆነ | 15 |
| 5 | ፈጠራውን ስለማባዛት እና ያለው ዘላቂነት<br><br>• በተቋማት/ኢንተርፕራይዞች መባዛት የሚችል ከሆነ<br><br>• ግልፅ የአሰራር መነሻ ስራ /prototype/ ያለው<br><br>• ዘላቂነት ያለው የፈጠራ ስራ | 10 |

አባሪ 7

## በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

## በሀገር አቀፍ የፈጠራ ስራ የሰሩ ግለሰቦችንና ተቋማትን ለመሸለም የተዘጋጀ የማመልከቻ ቅፅ

ፓ.ሳ.ቁ፡ 2490    ስልክ ቁጥር፡ 0118-962290 / 0911-477477 / 0913089655

ፋክስ፡ 011-4-66 02 41 / 011-4-169533

የኢሜል አድራሻ፡most@ethinet.et/innvmost@gmail.com

ዌብሳይት፡http:/www.gov.et

1.የዕጩ ተወዳዳሪው ግላዊ መረጃ

- ስም እስከ አያት፡-..........................................................................
- ፆታ፡- ወንድ...... ሴት.........
- አድራሻ፡-

ስልክ ቁጥር፡ የሞባይል፡..................... መደበኛ፡........................

ክልል፡-............................

ከተማ/ወረዳ፡-......................

ፋክስ ቁጥር፡-............................

ኢሜል፡-..................................

2.የትምህርት እና የስራ ሁኔታ

የትምህርት አይነት፡-............................

የትምህርት ደረጃ፡-............................

አሁን እየሰሩበት ያለው

ተቋም፡-.................

የስራ ሃላፊነት፡-..........

የስራ ልምድ፡-............

3.ለውድድር ያቀረቡት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፎች ውስጥ በሚከተለው ያመላክቱ

☐ በቴክኖሎጂና ኢንጂነሪንግ ሳይንስ

☐ በተፈጥሮ ሳይንስ

☐ በግብርና ሳይንስ

☐ በህክምና እና በጤና ሳይንስ

4.የፈጠራው/ስራው ርዕስ፡- ..........................................................................

5.የፈጠራው/ስራው ውጤት መግለጫ

የፈጠራ ተቋማት የሽልማት መስፈርቶች

ከዚህ በታች በተመላከተው ዝርዝር መስፈርት መሰረት የፈጠራ ተቋማት የስራ ውጤት ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

| ተ.ቁ | የመገምገሚያ መስፈርቶች | ለመስፈርቱ የተሰጠው ክብደት |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| 1 | የልዩ ፈጠራው አሰራር እና ጠቀሜታ | 50 |
| | i. ከማህበራዊ ጠቀሜታ አንፃር<br>• የህብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ የሚያሻሽል ከሆነ<br>• የገቢ ምንጭነት<br>• የስራ ዕድል የሚፈጥር ከሆነ<br>• ለሴችን እና ለአካል ጉዳተኞች አመቺ እና የስራ ጫናን የሚቀንስ ከሆነ | 15 |
| | ii. ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንፃር<br>• የገቢ ምርትን የሚተካ የፈጠራ ስራ ከሆነ<br>• የወጪ ምርትን የሚያሳድግ ፈጠራ ከሆነ | 20 |
| | iii. ከአካባቢ ልማትና ጥበቃ አንፃር<br>• አካባቢን ከመጠበቅና ከማልማት አንፃር<br>• ዘላቂነት ያለው የተፈጥሮ ሀብትን አጠቃቀም እና ማልማት | 15 |
| 2 | የቴክኖሎጂ አቅም<br>• የቴክኖሎጂው ተቀባይነት<br>• ቴክኖሎጂውን ከመረዳት አንፃር<br>• ቴክኖሎጂውን ከማላመድ አንፃር | 15 |

| | | |
|---|---|---|
| 3 | የጋራ ተጠቃሚነትን ከማስፋት አንፃር ያለው ትስስር<br>• ከአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች<br>• ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች<br>• ከማህበረሰብ ልማት ድርጅቶች<br>• በጋራ ምርምር (በሀገር ውስጥ/ በውጭ ሀገር)<br>• ከከፍተኛ ት/ት ተቋማት እና ቴ/ሙ/ት/ስ ኮሌጆች | 12 |
| 4 | የተቋማትን የስራ አመራር ብቃት ከማሳደግ አንፃር<br>• ደንበኛ ተኮር<br>• አመራር ሰጭነት<br>• የስራ ሂደት ፍሰት<br>• የአሰራር ስርአት ያለው<br>• ተከታታይነት ያለው መሻሻል<br>• አሳታፊነት | 6 |
| 5 | የፈጠራ ስራው ተደራሽነት /ስርጭት<br>• የፈጠራው ስራው ፕሮቶታይፕ/ሞዴል ያለው መሆኑ<br>• አውደ ርዕይ ላይ የቀረበ<br>• ሀገራዊ አውድ ጥናት ላይ የቀረበ<br>• ከሌሎች ተቋማት ጋር የትስስር ተሞክሮ ያለው<br>• ፈጠራውን በተለያዩ የሚዲያ ውጤቶች ያስተዋወቀ | 8 |

| | | |
|---|---|---|
| 6 | ለፈጠራ ስራው ያሉ አስቻይ /አበረታች ሁኔታዎች<br><br>• የሽልማት እና የማበረታቻ ስርአት መኖሩ<br><br>• የተመቻቹ የግብአት እና የመስረተ ልማት አቅርቦት መኖራቸው<br><br>• በዘርፉ ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች መኖራቸው | 9 |

አባሪ 8

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

በሀገር አቀፍ የሀገር በቀል ፈጠራ ስራ የሰሩ ግለሰቦችን ለመሸለም የተዘጋጀ የማመልከቻ ቅፅ

ፖ.ሳ.ቁ፡ 2490 ስልክ ቁጥር፡ 0118-962290 / 0911-477477 / 0913089655

ፋክስ፡ 011-4-66 02 41 / 011-4-169533

የኢሜል አድራሻ፡most@ethinet.et/innvmost@gmail.com

ዌብሳይት፡http:/www.gov.et

1.የዕጩ ተወዳዳሪው ግላዊ መረጃ

- ስም እስከ አያት፡-..........................................................
- ፆታ፡- ወንድ...... ሴት.........
- አድራሻ፡-

ስልክ ቁጥር፡ የሞባይል፡......................መደበኛ፡.......................

ክልል፡-.............................

ከተማ/ወረዳ፡-......................

ፋክስ ቁጥር፡-.............................

ኢሜል፡-...................................

2.የትምህርት እና የስራ ሁኔታ

የትምህርት አይነት፡-............................

የትምህርት ደረጃ፡-.............................

አሁን እየሰሩበት ያለው

ተቋም፡-.................

የስራ ሃላፊነት፡-..........

የስራ ልምድ፡-............

3.ለውድድር ያቀረቡት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፎች ውስጥ በሚከተለው ያመላክቱ

☐ በቴክኖሎጂና ኢንጂነሪንግ ሳይንስ

☐ በተፈጥሮ ሳይንስ

☐ በግብርና ሳይንስ

☐ በህክምና እና በጤና ሳይንስ

4.የፈጠራው/ስራው ርዕስ፡- ...............................................................................

5.የፈጠራው/ስራው ውጤት መግለጫ

የሀገር በቀል ፈጠራ የሽልማት መስፈርቶች

ከዚህ በታች በተመላከተው ዝርዝር መስፈርት መሰረት የሀገር በቀል ፈጠራ የስራ ውጤት ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

| ተ.ቁ | የሀገር በቀል ፈጠራው መስፈርት | ለመስፈርቱ የተሰጠው ዋጋ በፐርሰንት |
|---|---|---|
| 1 | የተወዳዳሪው የትምህርት ደረጃ<br>• የመጀመሪያ ዲግሪና በላይ<br>• ዲፕሎማ<br>• የ2ኛ ደረጃ ትምህርትን ያጠናቀቀ | 10<br>5<br>2<br>2 |

| | | |
|---|---|---|
| | • የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ያለው | 1 |
| 2 | ፈጠራው በማህበረሰቡ ያለው ተቀባይነት<br><br>• በጣም ከፍተኛ<br>• ከፍተኛ<br>• መካከለኛ | 10<br><br>5<br>3<br>2 |
| 3 | የሀገር በቀል የፈጠራ ስራው ይዘት<br><br>• ሙሉ በሙሉ ልዩና አዲስ<br>• የስራው ግብዓት ሙሉ በሙሉ በአካባቢው የሚሸፈን<br>• የፈጠራ ስራው ስርጭት ስፋት ወይም ተደራሽነት /ወደ ስራ የገባ | 20<br><br>8<br>6<br>6 |
| 4 | ለግኝቱ የተሰጠ ማረጋገጫ<br>• ለሀገር በቀል ፈጠራነቱ ከሚመለከታቸው ማረጋገጫ ያለው<br>• ከሚኖሩበት አካባቢ አስተዳደር አካል/ማህበረሰባዊ ተቋም ድጋፍ ያገኘ<br>• ከሚመለከተው መ/ቤት የባለቤትነት ሰርቲፊኬት/ማስረጃ ያለው | 15<br>6<br>5<br>4 |
| 5 | ለተጠቃሚዎችና ለአካባቢው ማህበረሰብ የሚሰጠው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ<br>• በጣም ከፍተኛ<br>• ከፍተኛ | 10<br><br>5 |

| | | |
|---|---|---|
| | • መካከለኛ | 3<br><br>2 |
| 6 | ፈጠራው በቴክኖሎጂ ለማባዛትና ለማሻሻል ያለው አቅም<br>• በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማዘመን የሚችል<br>• ለመረዳት ውስብስብ ያልሆነ<br>• የጥሬ ግብዓት በቀላሉና በአቅራቢያ የሚገኝ | 10<br>5<br>3<br>2 |
| 7 | የፈጠራው ስፋትና ተደራሽነት<br>• በሀገር አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ያለው<br>• በክልል ደረጃ  ዕውቅና ያለው<br>• በወረዳ/ዞን/አካባቢ ደረጃ እውቅና ያለው | 15<br>6<br>5<br>4 |
| 8 | የአጠቃቀምና የአሰራር ሁኔታና ስርጭት/ብዜት<br>• ግልፅ የሆነ የአዘገጃጀት/ የአጠቃቀምና የአሰራር  መመሪያ ያለው<br>• ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ መቅረብ የሚችል<br>• በቴክኖሎጂ ለማዘመንና ለማባዛት የሚያስችል | 10<br>4<br>3<br>3 |

አባሪ 9

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በሀገር አቀፍ የልዩ ተሰጥኦ ስራ ያላቸውን ለመሸለም የተዘጋጀ የማመልከቻ ቅፅ

ፓ.ሳ.ቁ፡ 2490    ስልክ ቁጥር፡ 0118-962290 / 0911-477477 / 0913089655

ፋክስ፡ 011-4-66 02 41 / 011-4-169533

የኢሜል አድራሻ፡most@ethinet.et/innvmost@gmail.com

ዌብሳይት፡http:/www.gov.et

1.የዕጩ ተወዳዳሪው ግላዊ መረጃ

- ስም እስከ አያት፡-........................................................
- ፆታ፡- ወንድ...... ሴት.........
- አድራሻ፡-

ስልክ ቁጥር፡ የሞባይል፡....................መደበኛ፡.......................

ክልል፡-.............................

ከተማ/ወረዳ፡-......................

ፋክስ ቁጥር፡-.............................

ኢሜል፡-..................................

2.የትምህርት እና የስራ ሁኔታ

የትምህርት አይነት፡-...........................

የትምህርት ደረጃ፡-.............................

አሁን እየሰሩበት ያለው

ተቋም፡-.................

የስራ ሃላፊነት፡-..........

የስራ ልምድ፡-............

3.ለውድድር ያቀረቡት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፎች ውስጥ በሚከተለው ያመላክቱ

☐ በቴክኖሎጂና ኢንጂነሪንግ ሳይንስ

☐ በተፈጥሮ ሳይንስ

☐ በግብርና ሳይንስ

☐ በህክምና እና በጤና ሳይንስ

4.የፈጠራው/ስራው ርዕስ፡- ..........................................................................

5.የፈጠራው/ስራው ውጤት መግለጫ

የልዩ ተሰጥኦ ስራ የሽልማት መስፈርቶች

ከዚህ በታች በተመላከተው ዝርዝር መስፈርት መሰረት የሀገር በቀል ፈጠራ የስራ ውጤት ነጥብ ይሰጠዋል፡፡

| ተ.ቁ | የልዩ ተሰጥኦ ስራው መስፈርት | ለመስፈርቱ የተሰጠው ዋጋ በፐርሰንት |
|---|---|---|
| 1 | የልዩ ተሰጥኦ አቅራቢው/ባለቤት የትምህርት ደረጃ | 10 |
| | • የመጀመሪያ ዲግሪና በላይ | 5 |
| | • ዲፕሎማ | 2 |
| | • የ2ኛ ደረጃ ትምህርትን ያጠናቀቀ | 2 |

| | | |
|---|---|---|
| | • የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ያለው | 1 |
| 2 | በሳ.ቴ ዘርፍ የልዩ ተሰጥኦው አይነትና ደረጃ<br>• የፈጠራ ወይም የምርት ተሰጥኦ/Product Innovation Talent<br>• የሳይንስ፣ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግና የሂሳብ ዕውቀት ተሰጥኦ/STEM Talent<br>• የአሰራር ክህሎት ተሰጥኦ /Technical Innovation Talent | 20<br>8<br>6<br>6 |
| 3 | ልዩ-ተሰጥኦው በዘርፉ (ተቋም/ት/ቤት/ ዩኒቨርሲቲ/ አካባቢው) ያለው ተቀባይነት<br>• በጣም ከፍተኛ(ሙሉ በሙሉ)<br>• ከፍተኛ(በከፊል)<br>• መካከለኛ(በተወሰነ) | 15<br>6<br>5<br>4 |
| 4 | የልዩ ተሰጥኦው ውህደት<br>• የፈጠራ ልዩ ተሰጥኦ (የፈጠራ፣ የክህሎትና የእውቀት)<br>• የዕውቀት ልዩ ተሰጥኦ (የፈጠራና የዕውቀት)<br>• የክህሎት ልዩ ተሰጥኦ (የክህሎት) | 15<br>6<br>5<br>4 |
| 5 | የልዩ ተሰጥኦው ቴክኖሎጂያዊና ሳይንሳዊ ይዘት<br>• ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂያዊ(ሙሉ በሙሉ)<br>• ሳይንሳዊ(በከፊል)<br>• ቴክኖሎጂያዊ (በተወሰነ) | 10<br>5<br>3<br>2 |

| | | |
|---|---|---|
| 6 | ለልዩ ተሰጥኦው የቀረበ ማረጋገጫ<br>• ከሚመለከተው ተቋም በዘርፉ የተሰጠ የምስክር ወረቀት/ ሰርቲፊኬት<br>• በሚገኙበት ተቋም/ድርጅት ደረጃ የተሰጠ የዕውቅና ማስረጃ<br>• ከሚኖሩበት የአካባቢ አስተዳደር አካል ወይም ት/ቤት ድጋፍ ያለው | 5<br>2<br>2<br>1 |
| 7 | ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ለዘርፍ የሚኖረው አስተዋጽኦና ፋይዳ<br>• በጣም ከፍተኛ<br>• ከፍተኛ<br>• መካከለኛ | 10<br>5<br>3<br>2 |
| 8 | የልዩ ተሰጥኦው ተደራሽነት<br>• በአለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ያለው<br>• በሀገር አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ያለው<br>• በተቋም/አካባቢ ደረጃ እውቅና ያለው | 5<br>3<br>1<br>1 |
| 9 | የልዩ ተሰጥኦው የአጠቃቀም ሁኔታና ደረጃ<br>• ግልፅ የሆነ የአዘገጃጀት/ ቀመር ያለው<br>• በዘርፉ መመዘኛ /መስኪያ ሊፈተሽ የሚችል<br>• በመስሎች ሊተገበር የሚችል | 10<br>4<br>3<br>3 |

አባሪ 10

የአመልካቾች ማጠቃለያ ዝርዝር መስፈርት

| ተ.ቁ | ጥቅል መስፈርቶች | ምልክት ያድርጉ | |
|---|---|---|---|
| | | አዎ | አይ/ደለም |
| 1 | ሙሉ በሙሉ የማመልከቻ ቅፁን ሞልተው አቅርበዋል? | | |
| 2 | ሙሉ አድራሻዎትን በመጠቀም የማመልከቻ ቅፁን በዝርዝር ሞልተዋል? | | |
| 3 | ግለ ታሪክ መረጃ በዝርዝር ተያይዟል? | | |
| 4 | የፈጠራ ውድድር መስፈርቱን በዝርዝር ሞልተዋል? | | |
| 5 | ከተቋም የተሠጠ የባለቤትነት/የግጋሎት ሞዴል ሰርትፊኬት እና አስፈላጊ ደጋፊ አስረጂ ሰነዶች ተያይዟል ? | | |
| 6 | ባለቤት ተቋም የፈጠራው/ስራው ውጤታማነትን/ ተቀባይነት የሚያረጋግጥ ማስረጃ ተያይዟል? | | |